# ካራማራና የቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ፍጻሜ

የካራማራ ድል ሲታሰብ ባለአንበሳው ዓርማ ቀደምት ሥፍራ ይይዛል። 3ኛ ክፍለ ጦር በአገራችን የጦርነት ታሪክ ላይ ትልቅ አሻራ ያሳረፈ ክፍል ነው። ክፍለ ጦሩ በሃገራችን ምስራቅና ሰሜን ክፍሎች ታላቅ የውጊያ ተጋድሎ ታሪክ ያለው ስለሆነ ታሪኩን በትክክል ለመረዳት የውጊያ ታሪክ ከሰራባቸው ቦታዎች አንጻር ስሙን በሁለት ከፍሎ ቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦርና ዳግማዊ 3ኛ ክ/ጦር ብሎ መሰየሙ ታሪኩን በየመልኩ ለማስቀመጥ ይረዳል። ቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ሐረር ላይ በ1939 ዓ/ም ተቋቁሞ መስከረም 1 ቀን 1970 ዓ/ም ካራማራ ላይ ሕልወናው አብቅቷል። ዳግማዊ 3ኛ ክ/ጦር ደግሞ ብ/ጀኔራል ይልማ ግዛው አዛዥ ሆነው ክ/ጦሩን ቆሬ ላይ በአዲስ መልክ እንዲያቋቁሙ መስከረም 4 ቀን 1970 ዓ/ም በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የተቋቋመ ሲሆን በአገራችን የሰሜኑ ክፍል የሚሰጠውን ግዳጅ የተወጣ በመጨረሻም መራኛ ላይ ሰኔ 8 ቀን 1982 ዓ/ም ተደምሶ ሕልውናው አክትሟል። ዳግማዊ 3ኛ ክ/ጦር በምስራቅ ግንባር ስለፈጸመው "የቆሬው ብረት አጥር" ብዬ ከትቤያለሁ፤ በሰሜኑ ግንባር ስለፈጸመው ገድል በዚያ ስላልነበርኩ የምለው የለኝም።

ቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር በብ/ጀኔራል አሰፋው ወ/ጊዮርጊስ አዛዥነት ጠቅላይ መምሪያውን ሐረር ላይ አድርጎ ሦስት ብርጌዶች ይዞ በ1939 ዓ/ም ተቋቋመ። ብርጌዶቹም፡- 9ኛ ብርጌድ ቀብሪደሃር ላይ ፤ 10ኛ ብርጌድ ጂጂጋና 11ኛ ብርጌድ ሐረር ላይ ነበሩ። 11ኛ ብርጌድ በኋላ ላይ ወደ ደጋሃቡር ተንቀሳቅሶ በቋሚነት እንዲሰፍር ተደርጓል። ክ/ጦሩ ሲመሠረት የአንበሳ ዓርማ መለያ ሆኖ የተሰጠው ሲሆን ማን እንደሰጠው የሚጠቁም ተጨባጭ መረጃ ባላገኝም ጀኔራል አማን አንዶም በ1953 ዓ/ም "የኦጋዴን አንበሣ" ብለው ሰይመውታል። የክ/ጦሩ ክፍሎች ብዛትና ቦታ አያያዝ በግንባሩ ያለውን ጠላት መቋቋም ለማስቻል እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየተለዋወጠ ቆይቷል።

ሶማሊያ ነጻ ስትወጣ ጀምሮ የተጠናወታት በኢትዮጵያ፤ በኬንያና ጅቡቲ ያሉ ሶማሊኛ ተናጋሪዎች ያሉበትን ቦታ በወረራ ይዞ " የታላቋ ሶማሊያ" ምስረታ ዕውን ለማድረግ ዝግጅት ስታደርግ ቆይታለች። በተለይም ፕሬዚዳንት መሐመድ ዚያድ ባሬ በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን ሲይዙ ሶሻሊዝም በማወጅ ከቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት ግንኙነት መሥርተው የመከላከያውን አቅም ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በተደረገላቸው ከፍተኛ የወታደራዊ ዕርዳታ በግንባር 3 ዕዞችና በመሃል ደግሞ ያልተሟሉ 2 ዕዞች አደራጅተዋል። በግንባር ያሉት 26ኛ ዕዝ በሰሜን ሶማሊያ ሐርጌሣ ላይ፤ 21ኛ ዕዝ በማዕከላዊ ሶማሊያ ዱስመሪብና 60ኛው ዕዝ በደቡብ ሶማሊያ ባይደዋ ላይ ሲሆኑ ተጠባባቂዎቹ ደግሞ 43ኛና 54ኛ ዕዞች በዋና ከተማዋ ሞቃዲሾ አካባቢ ነበሩ። ለግንዛቤ እንዲረዳ አንድ የሶማሊያ ዕዝ 2 እግረኛ ክ/ጦሮች፤ 1 ሜካናይዝድ ክ/ጦር፤ 1 ታንክ ብርጌድ፤ 1 መድፈኛ ብርጌድ፤ 1 አየር መቃወሚያ ብርጌድ፤ መሐንዲስና መገናኛ የመሳሰሉ ኪነታዊ ክፍሎችን የያዘ ነበር።

በኢትዮጵያ በኩል ቀደም ሲል በንጉሡ ጊዜ የነበረው የኃይል አሠላለፍ 3ኛ አምበሳው ክ/ጦር ጠቅላይ ሠፈሩን ሐረር ላይ አድርጎ፤ ጂጂጋ ላይ 10ኛ ሜ/ብርጌድ፤ ደጋሃቡር 11ኛ ብርጌድ፤ ቀብሪደሃር 9ኛ ብርጌድ፤ ጎዴ 5ኛ ብርጌድ ይዞ የምስራቁን ቀጠና ይጠብቅ ነበር። የሠራዊቱ የነፍስ ወከፍ ትጥቅ ኤም 1 (AM1)ና ካርባይን ነበሩ። በከባድ መሣሪያ በኩል የአሜሪካን ሥሪት 155ሚ/ሜት ተጎታች መድፍ ( 4ኛ መድፈኛ ሻለቃ ጂማ የነበረ በኋላ ድሬዳዋ የመጣ)፤ 105 ሚ/ሜትር ተጎታች መድግፍ ሻለቃ አማሬሳ ላይ ነበር ። በታንክ በኩል ናዝሬት የነበሩት ኤም 41ና ኤም 47 አሮጌ ታንኮችና ብረት ለበሶች ወደ ጂጂጋ ተወሰደው 10ኛ ብርጌድ እንዲታጠቃቸው ተደርጓል። ከነዚሁ ብረት ለበሶች ውስጥ ዋርደር ለነበረው 22ኛ ሻለቃ ተልኳል።

ከላይ የተጠቀሰው የሶማሊያ ጦርና የኢትዮጵያ ጦር የኃይል ሚዛን ሲነጻጸር የሶማሊያ ከፍተኛ የሆነ የበላይነት የሚያመለክት ነበር። በአየር ኃይልም እንዲሁ የኃይል የበላይነት ነበራቸው። ንጉሱም የበላይነቱን ለማስተካከል የሚያስችሉ የጦር መሣሪያዎች እንዲሸጥላቸው በአካል አሜሪካ ሄደው ጥያቄ አቀረቡ። አሜሪካም የንጉሱን ሥጋት በመጋራት የኃይል ሚዛኑን ለማስጠበቅ የሚያስችሉ በ1968 የሚከተሉትን ጦር መሣሪያዎች ለመሸጥ ተስማሙ። እነሱም M60 ታንክ፤ BGM-71 TOW (ፀረ- ታንክ ሚሳይል ማወንጨፊያ) ፤ M109 155 ሚ/ሜት ርዕሰ ውልብሊቢት (Self propelled) መድፍ፤ M14 የነፍስ ወከፍ መሣሪያ፤ M60 መትረየስ፤ M79 የቦንብ ማወንጨፊያ ሲሆኑ በአየር ኃይል በኩል ደግሞ F5-E ተዋጊ አውሮፕላኖችና TPS 43 D ሬዳር ነበሩ። ስምምነት የተደረገባቸው መሣሪያዎች በሙሉ ሳይገቡ ደርግ ንጉሡን አውርዶ ሥልጣን በመያዙ ሳይላኩ የቀሩ መሣሪያዎች አሉ፤ ለምሳሌ ቶው ሚሳይል አወንጫፊ ለ15 ተከፍሎ የገባው 5 ብቻ ሲሆን ሚሳይሉም ለያንዳንዱ 5 ጉርሻ ሂሳብ 15 ብቻ ነበር የገባው።

ከላይ ከተጠቀሱት መሣሪያዎች በተለይ ኤም60 ታንክ በወቅቱ ሶማሊያ ከታጠቀቻቸው የበላይ የሚያደርገው ሁለት መሠረታዊ ቴክኖሎጂ ያለው መሆኑ ነበር። ርቀት ለኪ (Range Finder) ነበረው፤ የታንኩ መድፉ ኢላማው ላይ ሲነጣጠር ርቀቱን ያሳያል ከዚያ ጥይት አጉርሶ መተኮስ ብቻ ነው። አይስትም። ሁለተኛው ደግሞ እንዳይነቃነቅ የሚያደርግ (Stabilizer) ነበረው። የታንኩ መድፍ ዒላማው ላይ ሲነጣጠር ታንኩ ወዴትም አቅጣጫ ቢነቃነቅ የታንኩ መድፍ ያለበት 360 ዲግሪ የሚዞረው (Turret) በዒላማው ላይ እንዳነጣጠር ይቆያል አይነቃነቅም። ይህ ማለት ታንኩ በንቅናቄም ላይ እያለ መተኮስ ይችላል። በወቅቱ የሶማሊያ ጦር የታጠቃቸው ታንኮች ከላይ የተጠቀሱት አልነበሯቸውም፤ ለመተኮስ መቆም አለባቸው፤ ዒላማን በመጀመሪያ ጥይት የመምታት አስተማማኝነት አልነበራቸው ምክንያቱም የዒላማው ርቀት በታንክ አዛዡ ግምት የሚሰጥ በመሆኑ። ከማወንጨፊያው ተተኩሶ በገመድ ወደ ዒላማው የሚመራው ታንክ አውዳሚው የቶው ሚሳይልም የሚስት አልነበረም። የመሣሪያዎቹ ጥራት ለድል እንደሚያበቁ ዕምነት ተጥሎባቸው ነበር።

እነዚህ መሣሪያዎች ተቀናጅተው ጠላትን መመከትና ብሎም ማጥቃት የሚቻልበት አሠላለፍ መሠረት ያደረገ አደረጃጀት እንደሚከተለው የታሰበ ነበር፤ አንድ ሞተራይዝድ ሻለቃ፤ አንድ ሜካናይዝድ ሻለቃ፤ አንድ ጸረ ታንክ ቶው ሻምበል፤ አንድ ታንክ ሻለቃና አንድ ተነቃናቂ መድፍ ሻለቃ ተቀናጅተው 100% ተነቃናቂና ከፍተኛ የተኩስ ኃይል ያላቸው በመሆኑ በምሥራቁ የአገራችን ሜዳማ የመሬት ገጽ ላይ ጠላትን መከላከል እንደሚያስችል ታስቦ ከአሜሪካ በመጀመሪያው ዙር በገቡት አዳዲስ የጦር መሣሪያዎች ማደራጀት ተጀመረ። በዚሁ መሠረት 33ኛ ሞተራይዝድ ሻለቃ ጭናክሰን ላይ፤ 9ኛ ሜካናይዝድ ሻለቃ፤ አዲሱን ኤም60 ታንክ የታጠቀ 3ኛ ሻለቃና ቶው ጸረ ታንክ የታጠቀ የሙቶ ጂጂጋ ላይ በ10ኛ ሜ/ብርጌድ ሥር የተደራጁ ሲሆን 4ኛ መድፈኛ ሻለቃ 155 ሚ/ሜትር ርዕሰ ውልብልቢት ታጥቆ ድሬዳዋ ላይ ተቋቋመ። የቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ክፍሎችም አዲሱን ኤም14 የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ታጠቁ። ቀደም ሲል ለሥልጠና አሜሪካ የተላኩ መኮንኖች ተመልሰው ከአሜሪካና እስራኤል ወታደራዊ ሞያተኞች ጋር ተቀናጅተው ለጦሩ ሥልጠናው መሰጠት ተጀመረ።

ሁኔታው በዚህ መልክ እያለ በአገሪቱ በተነሳው ነውጥ ደርግ ተቋቁሞ ንጉሱን አውርዶ ሥልጣን ያዘ። አሜሪካም በሁለተኛው ዙር ሊመጣ የታቀደውን መሣሪያ አገደች። የደርግን አገዛዝ ያልተቀበሉ በውስጥም በውጪም ያሉ ተቃዋሚዎች በደርግ,ላይ ተነሱ። ይህን ተቃውሞ ለመቋቋም የደርጉ ሊቀመንበር ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም ከነበሩበት ቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር በእሳቸው ዕውቅና ወደ መሐል አገር ጦር እንዲንቀሳቀስ ታዘዘ።

ጂጂጋ ከነበረውና በሶማሌዎችም ዘንድ በጣም ይፈራ ከነበረው 10ኛ ሜ/ብርጌድ ውስጥ ጭናክሰን የነበረው 33ኛ ሞተራይዝድ ሻለቃ በሙሉ፤ ከ9ኛ ሜ/ሻለቃ ሁለት ሜካናይዝድ ሻምበሎች(1 ሻ/ል አ/አ ቤተመንግሥት ጥበቃ፤ 1 ሻ/ል ኤርትራ)፤ ከ3ኛ ታንክ ሻለቃ 1 ሻምበል (አ/አ ቤተመንግሥት ጥበቃ) ሲወሰዱ ጂጂጋ ላይ የቀረ የብርጌዱ ጠቅላይ ሠፈር፤ አንድ ሜካናይድ ሻምበል ፤ 2 ታንክ ሻምበሎች እና አንድ የሙቶ ቶው (5 ማውንጨፊያ ያለው) ብቻ ነበር።

ደጋሃቡር የነበረው 11ኛ እግረኛ ብርጌድ ሁለት እግረኛ ሻለቆች ነበሩት፤ 25ኛ እግረኛ ሻለቃ ደጋሃቡር ላይና 40ኛ እግረኛ ሻለቃ አቡዋሬ ላይ ነበሩ። 25ኛ ሻለቃ ወደ መሃል አገር ተወሰደ። በብርጌዱ ቀጠና የቀረ አቡዋሬ 40ኛ ሻለቃ፤ ደጋሃቡር የብርጌዱ ጠቅላይ ሠፈር ወታደሮችና 250 ምልምሎች ነበሩ።

ጎዴ ላይ የነበረው 5ኛ ብርጌድም ሁለት እግረኛ ሻለቆች ነበሩት፤ 6ኛና 14ኛ። 6ኛ እግረኛ ሻለቃ ወደመሃል አገር ሲወሰድ ጎዴ የቀረ የብርጌዱ ጠቅላይ ሠፈርና አንድ ሻለቃ ጦር ብቻ ነበር።

ቀብሪደሃር ላይ ከነበረው 9ኛ እግረኛ ብርጌድ ጦር አልተወሰደበትም ሆኖም በዕዙ ሥሩ 4 ሻለቆች የነበሩ ሲሆን ቀጠናው ሰፊ ስለነበር ተበታትነው እርስ በርስ መረዳዳት በማይችሉበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር የሠፈሩት፤ 3ኛ ሻለቃ ገላዲን፤ 5ኛ ኮማንዶ ሻለቃ ሙስታሂል፤ 18ኛ ሻለቃ ቀብሪደሃር፤ 22ኛ ሜ/ሻለቃ ዋርደር ላይ ቀደምሲል ጀምሮ የሠፈሩ ነበሩ።

ድሬዳዋ ላይ አንድ እግረኛ ሻለቃና አንድ መድፍ ሻለቃ ነበሩ። እነሱም 7ኛ እግረኛ ሻለቃና 155 ሚ/ሜትር ርዕሰ ውልብሊቢት (SELF PROPELLED) የታጠቀው 4ኛ መድፈኛ ሻለቃ ነበሩ። 4ኛ መድፈኛ ሻለቃ (ገስጥ በሚል ስያሜ) ወደ መሃል አገር ተወሰደ።

ስለዚህ በቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ቀጠና የሶማሊያ ጦር ሠተት ብሎ እንዲገባ በሩ ክፍት ተደርጎለት ነበር ለማለት ያስደፍራል። የአገሪቱ መሪ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማሪያም በቀዳማዊው 3ኛ ክ/ጦር ውስጥ ለረጂም ጊዜ ሲያገለግሉ የቆዩ በመሆናቸው

ከላይ የተጠቀሰውን ጦር በእሳቸው ይሁንታ ከቀጠናው ሲነሳ የሶማሊያ ጦር ማጥቃት እንደሚሰነዝር ከማንም የበለጠ ግንዛቤው ነበራቸው። ታዲያ ቅድሚያ መሰጠት የነበረበት ለአገር ወይስ ለሥልጣን? ፍርዱን ለአንባቢ እተዋለሁ። ለሶማሊያው ወረራ ደርግና አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች መከላከያን አልገነቡም ሲሉ ንጉሡን ተጠያቂ ያደርጋሉ፤ ከላይ የተጠቀሰው መረጃ ግን ከንጉሡ ይልቅ ወደ ደርግ አመልካች ሆኖ ይታያል።

በማዕከላዊ ሶማሊያ ዱስመረብ ላይ የነበረው የሶማሊያ 21ኛው ዕዝ በሰኔ 5 ቀን 1969 ማጥቃት ጀምሮ ጎዴ፤ ቀብሪደሃና ደጋሃቡር የነበሩ ብርጌዶችን በአጭር ጊዜ ደምስሶ ቀጠናውን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረ። ቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ከነበሩት አራት ብርጌዶች ውስጥ የቀረው አንድ ብቻ ሲሆን እሱም ጂጂጋ የሚገኘው 10ኛ ሜ/ብርጌድ ነበር።

ሐርጌሣ ላይ የሚገኘው የሶማሊያ 26ኛ ዕዝ ደግሞ ጂጂጋ፤ ድሬዳዋና ሐረር ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ጦር ደምሶ ቦታዎቹን እንዲይዝ በተሰጠው ግዳጅ መሠረት ጂጂጋን ማጥቃት ጀመረ። 10ኛ ብርጌድን በመድፍ ሲደበድብ ቆይቶ የተቀናጀ ማጥቃት ሠንዝሮ ከተማዋን መያዝ አልቻለም። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሁኔታውን ተረድቶ መመሪያ ለመስጠት ነሐሴ 13 ቀን 1969 ዓ/ም ጂጂጋ ደርሰው በብርጌዱ አዛዥ በሌ/ኮሎኔል ኃይሌ ተሰፋሚካኤል በተደረገው ገለጻ የኃይል እጥረት ስላለ ጂጂጋ ከተማ ተለቆ ካራማራ ላይ እንከላከል የሚል ሃሳብ ቀርቦላቸው ነበር። እሳቸውም ጂጂጋ ስትራቴጂክ በመሆኑ ከተማውን እንዳትለቁ ተከላከሉ የሚል መመሪያ ሰጥተው በዕለቱ ተመለሱ።

ጂጂጋ ለጥባለ ሜዳ ላይ የተቆረቆረች ከተማ ናት። ከከተማው በስተምዕራብ 5 ኪ/ሜትር ርቀት ላይ አንድ ብቻ የተሽከርካሪ ማለፊያ በር ያለው (ማርዳ ፓስ) ከሰሜን ወደ ደቡብ እንደ አጥር ሆኖ የተዘረጋ የካራማራ ተራራ አለ። ካራማራ ለመከላከል ውጊያ ምቹ የሆነ ስትራቴጂክ ቦታ ነው። ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ቀደምሲል ከቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ግንባር ኃይል በማንሳት ለሶማሊያ ማጥቃት ምቹ ሁኔታ እንደፈጠሩ ሁሉ አሁን ደግሞ ከተማው ተለቆ በአለው አነስተኛ ኃይል ካራማራ ላይ መከላከል እንዲደረግ የቀረበላቸውን ሃሳብ አለመቀበላቸው ለ10ኛ ብርጌድ በቀላሉ መደምሰስና ካራማራም በጠላት እጅ እንዲወድቅ ያደረገ ሁለተኛ ትልቅ ስተት ነበር።

የሶማሊያ 26ኛው ዕዝ ጦር በጂጂጋ ዙሪያ መከላከል በያዘው 10ኛ ሜ/ጦር ላይ ማጥቃቱን ቀጥሎ ወገንም በጀግንነት ቢከላከልም የሶማሊያ ጦር በነበረው የበላይነት ብርጌዱን ደምሶ መስከረም 1 ቀን 1970 ዓ/ም ካራማራን ይዟል።

በቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ዕዝ ሥር የነበሩ 4 ብርጌዶች በሙሉ ተደምሰው የቀረው ሐረር ላይ የነበረው ጠቅላይ መምሪያው ነበር፤ እሱም ተጠናክሮ የምሥራቅ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ እንዲሆን በመደረጉ የቀዳማዊ 3ኛ ክ/ጦር ሕልውና ከካራማራ መያዝ ጋር አብሮ መስከረም 1 ቀን 1970 ዓ/ም አክትሟል።

አሁን አገራችን ያለችበት ጠቅላላ ሁኔታ ሲጤን በሶማሌ ጊዜ ከነበረው ጋር ይመሳሰላል፤እንዲያውም የአሁኑ የከፋ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ አደዋውና ካራማራ መጪውንም በድል ይወጣዋል፤ ግን ለድል ቁልፉ አንድነት መሆኑን መገንዘብ ያሻዋል።

GC 656